Legal Aid Society
OF THE DISTRICT OF COLUMBIA
MAKING JUSTICE REAL

# በኮቪድ-19 የወረርሽኝ አደጋ ወቅት፤
# ከስራ ሲወጡ በዲስትሪክቱ ስለሚሰጠው ክፍያ
## (ግንቦት 11 ቀን 2020 የተሻሻለ)


ብቁነት

- በኮቪድ-19 ምክንያት ስራዬን (ወይም ከገቢዬ ትልቁን  ክፍል) አጣሁኝ፤ ከስራ የመውጣት ክፍያ ለማግኘት ብቁ ነኝን?
- የአሜሪካ ዜጋ አይደለሁም፤ ዘላቂ የሆነ በአገሪቱ የመቀመጥ ወረቀትም የለኝም፤ ከስራ የመውጣት ክፍያ ለማግኘት ብቁ ነኝን?

ማመልከቻዎች

- እንዴት ነው የማመለከተው?
- ኮምፑተር ባይኖረኝም ለማመልከት እችላለሁን ?
- የመጀመርያዬን ማመልከቻ አስገባሁ  ግን እስከአሁን እንደተቀበሉኝና እንዳልተቀበሉኝ አላወኩም፤ በዚህ መልስ በምጠብቅበት ወቅት ማድረግ የሚገባኝ ሌላ ነገር አለን ?
- የመጀመርያ ማመልከቻዬን ካስገባሁ ሳምንታት አለፉ ግን እስከአሁን የተከፈልኩት ምንም ነገር የለም። ምን ላድረግ ?
- በፖስታ አንድ “ ግንዘባዊ ውሳኔ” የሚል ደብዳቤ አገኘሁ። ምን ማለት ነው?
- መጀመርያ ያስገባሁት ማመልከቻ ተቀባይነት ባያገኝስ ?

የክፍያው ልክ

- በዚህ የስራ መውጣት ክፍያ ምን ያህል ነው የማገኘው ?
- እስከ መቼ ነው ይህን ክፍያ መከፈል የምቀጥለው ?
- የስራ ቦታዬ እንደገና ተከፍቷል፤ እኔ የምስራው ግን በከፊል  ግዜያት ነው (part-time) ነው፤ አሁንም የስራ መውጣት ክፍያ ለማግኘት ብቁ ነኝን ?
- ይህንን ከስራ የመውጣት ክፍያ ማግኘቴ ሌሎች የማገኛቸውን ክፍያዎች ለምሳሌ እንደ ስናፕ (SNAP) ወይም ሜዲኬድ( Medicaid?) የመሳሰሉትን ሊነካቸው ይችላልን ?

ከልክ በላይ ሲከፈል (Overpayments)

- ከስራ የመውጣት ክፍያዬ ቀደም ሲል የተደረገውን ከልክ በላይ ክፍያ መልሶ ለመክፈል እየተወሰደብኝ ነው ። ምን ላድርግ ?

ህዝባዊ ክፍያ

- ከስራ የመውጣት ክፍያ (unemployment benefits) እንዲከፈለኝ ባመለከት፤ ካለው የህዝባዊ ክፍያ ህግ ጋር ይጋጭብኛልን ?

**<u>ብቁነት</u>**

**በኮቪድ-19 (COVID-19) ምክንያት ስራዬን (ወይም ከገቢዬ ከፍተኛውን ክፍል) አጣሁኝ። ከስራ ለወጡ የሚከፈል ክፍያ (unemployment benefits) ለማግኘት ብቁ ነኝን?**

እርስዎ በዲስትሪክቱ ይኑሩ አይኑሩ፤ የስራዎ ቦታ ግን በዲስትሪክቱ ውስጥ ከሆነ፤ ከስራ የወጡት በእርስዎ ጉድለት ካልሆነ፤ ስራ ለመስራት አቅሙም ፍላጎቱም ካሎት፤ ወይም እየሰሩ ቢሆኑም የሚሰጦት ክፍያ ግን ከቀድሞው በሰዓትም ሆነ በገንዘብ ከጎደለ፤ በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ከስራ ለወጡ የሚከፈለውን ክፍያ ለማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ።

በሌላ ክፍለሃገር ከስራ ለወጡ የሚከፈለውን ክፍያ( unemployment benefits) ለማግኘት እንዴት ማመልከት እንደምትችሉ የሚያስረዳ መረጃ ለማግኘት እዚህ here የሚለውን ይጫኑ።

ይህንን ከስራ ለወጡ የሚከፈለውን ክፍያ( unemployment benefits) ለማግኘት ብቁ የማይሆኑት (1) በአሜሪካን አገር ስራ ለመስራት የስራ ፍቃድ ከሌሎት (2) ከስራ የወጡት በራስዎ ጉድለት ከሆነ ወይም (3) ስራ ለመስራት ጉልበቱም ፍላጎቱም ከሌሎት ብቻ ነው። ሆኖም ግን በኮቪድ-19 (COVID-19) ወረርሽኝ በሽታ ተጠቅተው የታመሙ ከሆነ፤ በዚህ በሽታ ምክንያት ከቤት እንዳይወጡ ወይም ከሰው ጋር እንዳይገናኙ በሓኪም ከታዘዘሎት፤ ወይም በዚህ በሽታ የተጠቃን ሰው የሚንከባከቡ ከሆነ፤ ወይም በዚህ በኮቪድ-19 (COVID-19) ምክንያት ትምህርት ቤቶች ከተዘጉና ልጆች ትምህርት ቤት መሄድ የማይችሉ ከሆነና የህጻናት መዋያ ቦታዎችም ከተዘጉና እርስዎ ልጆቹን ለመጠበቅ ከተገደዱ ክፍያውን ለማግኘት ብቁ ይሆናሉ።፡

**እኔ የአሜሪካን ዜጋ አይደለሁም፤ ዘላቂ የመኖርያ ወረቀትም የለኝም። የስራ መውጣት ክፍያውን (unemployment benefits) ለማግኘት ብቁ ነኝን?**

ምናልባት። እንደ አንድ ስደተኛ፤ መደበኛውን ከስራ የመውጣት ክፍያን ለማግኘት፤ በአሜሪካን አገር ስራ ለመስራት የሚፈቅድ ወረቀት ማግኘት አለቦት። በሚከተሉት ወቅቶች፤

1. ክፍያውን ለማግኘት የመጀመርያ ማመልከቻዎን ሲያስገቡ
2. ክፍያዎን ለማግኘት፤ በየሳምንቱ "ሳምንታዊ የጥያቄ ካርዶችን" ሲሞሉ
3. የመጀመርያው ክፍያ እንዲከፈሉት ካመለከቱበት ዕለት ከ 12 እስከ 18 ወራት **በፊት** "መሰረታዊ ወቅት" በመባል የሚታወቀው የመጀመርያዎን ማመልከቻ ካስገቡ

የሚከተሉት የስደተኛ ቡድኖች ከስራ ሲወጡ ለሚከፈለው ክፍያ ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። ከብዙዎቹ ጥቂቶቹ፣ ጊዜያዊ የጥበቃ ፈቃድ ያላቸው (Temporary Protective Status)፣ በልጅነታቸው ወደ አገር የመጡ ልጆች (Deferred Action for Childhood Arrival (DACA)፣ ስደተኞች፣ ወይም መንግስት በስደተኛነት እንዲቀበላቸው ማመልከቻ ያስገቡ ሰዎች፣ ለተመላከተው ግዜ **ስራ ለመስራት የስራ ፍቃድ የተሰጣቸው እስከሆኑ ድረስ** ለዚህ ከስራ ሲወጣ ለሚሰጠው ክፍያ ብቁ ናቸው።

የአሜሪካን የስራ ሚኒስቴር (U.S. Department of Labor)፤ ስለዚሁ **በወረሽኝ ግዜ ስለሚደረገው ከስራ**

**የመውጣት ክፍያ**( Pandemic Unemployment Assistance (PUA) ና ስደተኞችን በተመለከተ ያለው ህግ ምን እንደሆነ ገና አላብራራም። ( ከወደታች እንደሚታየው below ልምዳዊ ያልሆኑ ሰራተኞች እንዴት የስራ ማቆም ክፍያ ማግኘት እንደሚችሉ በዝርዝር የሚጠቁም አዲስ፤ ግዜያዊ ፕሮግራም አውጥቷል)። በአሁኑ ግዜ ግን ዲስትሪክቱ፤ በወረርሽኙ አደጋ ምክንያት መደበኛውን የስራ መውጣት ክፍያ ለማግኘት የሚያመለክቱ ሰዎች፤ ክፍያውን ለመቀበል ብቁ የሚያደርጋቸውን መመዘኛ ስደተኞችም ያንኑ የብቁነት መመዘኛ እንዲከተሉ እያደረገ ነው።

**የህዝባዊ ክፍያዎች** ህጎች ከስራ መውጣት ጋር የሚደረግ ክፍያን አይመለከትም።

**ማመልከቻዎች**

**እንዴት ነው የማመለከተው?**

ባላፉት ከ15 እስከ 18 ወራት ውስጥ በሰሯቸው የስራ ዓይነቶች ላይ በመመርኮዝ በሁለት ዓይነት መንገዶች ሊያመለክቱ ይችላሉ፤

**መደበኛው የስራ ማጣት ክፍያ የሚመለከተው መደበኛ** (traditional**) ሰራተኞችን ነው-** ይህም ማለት ባለፉት ከ15 እስከ18 ወራት ውስጥ፤ ብቁ የሚያደርጋቸውን ገቢ ያገኙና በአሰሪ ዘንድ ተቀጥረው የግብር መክፈያ ፎርም( W-2s ) የሚያገኙ ናቸው። በኦንላይን online በመግባት (ዌብሳይቱ ደግሞ በእንግሊዘኛ ወይም በስፓኒሽ ቋንቋ የተዘጋጀ ነው) ወይም በስልክ ቁጥር (202) 724-7000 በመደወል ሊያመለክቱ ይችላሉ።.
ኮምፑተር ወይም ስማርትፎን (smartphone) ካሎት በኦንላይን እንዲያመለከቱ እንመክራለን ምክንያቱም በስልክ ከሆነ የረጅም ግዜ ጥበቃ ያስፈልገዋል።

የስራ አገልግሎት ሚኒስቴር (DOES) መደበኛውን የስራ ማጣት ክፍያ( standard unemployment benefits) ለማግኘት እንዴት ማመልከት እንደሚቻል ተጨማሪ መረጃ ያለው **ቀልጣፋ መመርያ** አውጥቷል።

**መደበኛ ሰራተኞች ላልሆኑትም፤ የወረሽኝ በሽታ የስራ ማጣት እርዳታ** (Pandemic Unemployment Assistance) **ወይም ፒ-ዩ-ኤ (PUA) የተባለ አዲስ የመንግስት ግዚያዊ ፕሮግራም አውጥቷል።**

ይህ ፕሮግራም፤ በኮንትራክት ተቀጥረው የሚሰሩ ሰራተኞችን፡ የራሳቸው ስራ ያላቸውን ሰዎች እንዲሁም እየተጠሩ በግዚያዊነት የሚሰሩ ሰራተኞችን (gig workers )፤ እንዲሁም መደበኛውን የስራ ማጣት ክፍያ ለመቀበል ብቁ ያልሆኑ ለምሳሌ ብቁ ሊያደርጋቸው የሚያስችል በቂ ገቢ ገና ማግኘት ያልጀመሩ፤ በ ኮቪድ-19 (COVID-19) ምክንያት ትምህርት ቤቶችና የህጻናት መዋያዎች ስለተዘጉና እነሱም ልጆች መጠበቅ ስላሏቸው ስራ መስራት ያልቻሉ ሰዎችን ያገለግላል። ኦንላይን **online** በመግባት (ይሄኛው ግን ዌብሳይቱ በእንግሊዘኛ ቋንቋ ብቻ የሆነ) ማመልከት ይችላሉ። የዚህ ማመልከቻ የመጀመርያው እርምጃ የስራ ማጣት ክፍያ እንዲሰጦት ማመልከትና ለመደበኛው ክፍያ ብቁ እንዳልሆኑ ማወቅ ነው።

የስራ አገልግሎት ሚኒስቴር (DOES) ስለዚሁ በወረሽኝ በሽታ ምክንያት ስለሚደረገው የስራ ማጣት ክፍያ የጥያቄና መልስ **FAQ** መረጃ አዘጋጅቶ አቅርቧል።

**ኮምፑተር ባይኖረኝም፤ ለማመልከት እችላለሁን?**

ለመደበኛው የስራ መውጣት ክፍያ በስልክ ቁጥር (202) 724-7000 በመደወል በስልክ ማመልከት ይችላሉ። ኮምፑተር ከሌሎትና በኦንላይን ማመልከት ካልቻሉ ወደ ሊጋል ኤድ( Legal Aid) በስልክ ቁጥር(202) 628-1161 በመደወል ሊረዱ ይችላሉ። ኮምፑተር ከሌሎትና በስልክም ሊገናኙ ካልቻሉ በ online ወደ ሊጋል ኤድ በመግባት ነጻ ህጋዊ አገልግሎት ለማግኘት አመልክቱ።

የሚያሳዝነው ለፐ-ዩ-ኤ( PUA ) ወይም በኮቪድ-19 ምክንያት ከስራ ለወጡ የሚደረግ የክፍያ ማመልከቻ በኦንላይን ብቻ ነው ያለው። ይህም አንዳንድ ዶኩመንቶችን ( ለምሳሌ ስላለፈው ገቢዎ የሚያስረዳ ዶኩመንት፤ በኮቪድ-19 (COVID-19) ምክንያት ስራዎን እንዳጡ ወይም ገቢዎ እንደቀነሰ የሚያረጋግጥ ማስረጃ) ማቅረብ የማመልከቻው አንድ አካል ነው። በእጅ ስልኮም ማመልከቻውን ለመሙላትና ለማስገባት መሞከር ይችላሉ። በእጅ ስልኮ ይህንን ሁሉ ማሟላት ካልቻሉ ግን ከ ሊጋል ኤድ (Legal Aid) ጋር ተነጋገሩ፡.

**የስራ መውጣት ክፍያ እንዲሰጠኝ የመጀመርያውን ማመልከቻ አስገብቻለሁ። እስከአሁን ድረስ ግን ተቀብለውኛል ወይስ አልተቀበሉኝም የሰማሁት ነገር የለም። የማመልከቻዬን መልስ እስካገኝ ድረስ ሌላ መውሰድ ያለብኝ እርምጃ አለን?**

በመደበኛው ፕሮግራምም ሆነ በፐ-ዩ-ኤ( PUA ) በኩል፤ ክፍያ ለማግኘት ያመለከቱ ሰራተኞች ሁሉ፡ በየሳምንቱ **"ሳምንታዊ የጥያቄ ካርድ"** (weekly claim card) ወይም ሳምንታዊ **"ቀጣይ የጥያቄ ካርድ"** (continued claim form) በመባል የሚታወቀውን በየሳምንቱ እየደውሉ ማሳወቅ ግዴታ አለባቸው።

የክፍያ ማግኘት ማመልከቻውን አንዴ ከሞሉና ካስገቡ በኋላ፤ እነኚህን ካርዶች በፖስታ ማግኘት ይጀምራሉ። ኮምፑተር ወይም ስማርትፎን ካሎት፤ እነዚህን ካርዶች በኦንላይን online ቢሞሏቸው ይመረጣል። በስልክ ቁጥር 202) 724-7000 በመደወልም መረጃውን መስጠት ይችላሉ ወይም ካርዶቹን ሞልተው በፖስታ መላክ ይችላሉ (ይህ ግን ብዙ የሚመረጥ አይደለም)። አንዴ ያስገቡት ማመልከቻ ተቀባይነት ካገኘ በኋላ፤ ክፍያ ማግኘት እስከፈለጉበት ቀን ድረስ፤ እነዚህን ካርዶች እየሞሉ መላክ ይችላሉ። በአጠቃላይም የ ስራ ማጣት ክፍያ ጽህፈት ቤት( DOES) ካርድ ላልተሞላለት ወይም ካርድ ላልተላከበት ሳምንት ክፍያ አይሰጥም።

ካርዱን በተመለከተ ከ ዲ-ኦ-ኢ-ኤስ (DOES) የተሰጠ ዝርዝራዊ መግለጫ ለመመልከት ይህንን here ይጫኑት።

**የስራ መውጣት ክፍያ እንዲሰጠኝ ካመለከትኩ ሳምንታት አለፈውኛል ። እስከአሁን ድረስ ግን ምንም የተከፈለኝ ገንዘብ የለም፤ ምን ማድረግ አለብኝ?**

እንደደንቡ ከሆነ፤ ማመልከቻዎን ካስገቡበት ዕለት ጀምሮ፤ ክፍያ ማግኘት ለመጀመር በግምት 21 ቀናት ይፈጃል። ካመለከቱ በ7 እና 10 ቀናት ውስጥ ግን በፖስታ አንዳንድ ወረቀቶችን ማግኘት ይጀምራሉ።

ከእነዚህ ሁለት ቀናት ውስጥ ምንም ሳይደርሶት አንዱም ቢሆን ካለፈ ግን በስልክ ቁጥር (202) 724-7000 ወደ ዲ-ኦ-ኢ-ኤስ (DOES) ደውለው ከማመልከቻ መርማሪዎች (claims examiner )ጋር መነጋገር እፈልጋለሁ ይበሉና ስለማመልከቻዎ ይጠይቁ። በሚከተለው አድራሻም does@dc.gov ወይም covid19.ui@dc.gov ወደ ዶስ ኢሜል ሊጽፉ ይችላሉ ። በኢሜልም ሆነ በስልክ ከዶስ ጋር መገናኘት ካልቻሉ፤ በስልክ ቁጥር (202) 628-1161 ወይ በኢሜል ወደ online በመግባት ከሊጋል ኤድ( Legal Aid) ጋር ለመገናኘትና ነጻ ህጋዊ ምክር ለማግኘት አመልክቱ።

**በፖስታ "ገንዘባዊ ውሳኔ"** (monetary determination) **የሚል ፎርም አገኘሁ። ይህ ምን ማለት ነው?**

"የገንዘባዊ ውሳኔ ማስታወሻ" (Notice of Monetary Determination)፤ **የስራ አገልግሎት ሚኒስቴር** (DOES) የሚልከው ፎርም ሆኖ፤ በሳምንት የሚያገኙትን ክፍያ፤ በአጠቃላይ የሚያገኙት የክፍያ ልክ፤ ይህንን ለመወሰን ግምት ውስጥ የገባው የገቢዎ መጠን እንዲሁም ያስገቡትን ማመልከቻ በሚመለከት መረጃዎችን ያጠቃለለ ነው።

በዚሁ ማስታወሻ ላይ አንድ ሳጥን አለ። በዚህ ሳጥን ውስጥም ይህንን ክፍያ ለማግኘት ብቁ ኖት ወይ አይደሉም በማለት ምልክት ያደርጋል። ብቁ አይደሉም የሚል ከሆነ፤ ለምን ብቁ እንዳልሆኑ የሚያስረዳውን መረጃ በጥንቃቄ ይመልከቱ። ምክንያቱም ብቁ አይደሉም የሚለው መረጃ ስህተት ሊሆን ይችላልና። ከዛ በኋላ ምን ማድረግ እንዳለቦት ለመረዳት፤(**መጀመርያ ያቀርብኩት ጥያቄ ተቀባይነት ካለገኘስ?)** የሚለውን ጥያቄ ይመልከቱ።

"ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ ወይም ብቁ አይደሉም" የሚለውን ጥያቄ የሚመልስ ደግሞ ሌላ የተመላከተ ሳጥን አለ። ፎርሙ ላይ ክፍያ ለማግኘት ብቁ ኖት የሚል ቢሆንም፤ ብቁ የማያደርጎት ችግር ሊኖር ይችላል የሚል ጽሁፍ የታከለበት ሊሆን ስለሚችል፤ ፎርሙን በጥንቃቄ ያንብቡት። የብቁነት ችግር ሊኖር ይችላል ማለት ደግሞ ክፍያውን ለማግኘት ብቁ አይደሉም ማለት አይደለም፤ ግን የስራ አገልግሎት ሚኒስቴር (DOES) ማመልከቻዎን ለማጠናቀቅ ተጨማሪ መረጃ ማግኘት እንደሚያስፈገውና ከእርሶ ጋር በመነጋገር መረጃውን ማግኘት እንደሚችል የሚጠቁም ነው።

**መጀመርያ ያስገባሁት ማመልከቻ ተቀባይነት ባያገኝስ?**

አመልካቾች፤ የመጀመርያ ማመልከቻቸውን ካስገቡ በኋላ፤ ከስራ አገልግሎት ሚኒስቴር( DOES) አያሌ ዶኩመንቶችን በፖስታ ያገኛሉ። ይሁንና ሁለት ዶኩመንቶች ብቻ ናቸው ማመልከቻው ተቀባይነት እንዳገኘና እንዳላገኘ የሚገልጹት። እነሱም አንደኛ **የገንዘብ ውሳኔ** ( Monetary Determination) ሲሆን ይህም የሰራተኛው ያለፈ የገቢ መጠን ግምት ውስጥ ገብቶ፤ የስራ ማጣት ክፍያ ለማግኘት ብቁ ነው ወይስ አይደለም የሚል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ **ማመልከቻዎችን የሚመረምር አካል የሰጠው ውሳኔ** (Determination by Claims Examiner) ነው። ይህም ከምርመራው በኋላ የተሰጠውን ውሳኔ የሚያስረዳ ነው።

**የገንዘብ ውሳኔው** ( Monetary Determination) መደበኛውን የስራ ማጣት ክፍያ (unemployment benefits ) ለማግኘት "ብቁ አይደለም" ብሎ ካስቀመጠ፤ መጀመርያ፤ በገባው የወረርሽኝ በሽታ ምክንያት የሚሰጠውን የስራ ማጣት ክፍያ (Pandemic Unemployment Assistance ወይም ፒ-ዩ-ኤ PUA) ለማግኘት ለማመልከት ብቁ መሆንዎን ያረጋገጡ። መጀመርያ የስራ ማጣት ክፍያ (unemployment benefits) ለማግኘት ያመልክቱ፤ ከዛ፤ ለዚህ ብቁ አይደሉም የሚለው የገንዘብ ውሳኔው (Monetary Determination) ሲደርሶት ነው በወረርሽኝ በሽታ ምክንያት የሚሰጠውን የስራ ማጣት ክፍያ( Pandemic Unemployment Assistance ወይም ፒ-ዩ-ኤ PUA ለማግኘት የሚያመለክቱት። እንዴት ማመልከት እንደሚችሉ ለማወቅ ከላይ የተጻፈውን እንዴት ነው ማመልከት የምችለው "How do I apply?" የሚለውን ክፍል ይመልከቱ።

ይሁንና በድንገተኛው የወረርሽኝ በሽታ ምክንያት ለሚደረገው ክፍያ ብቁ ሆነው ካልተገኙና የተደረሰው የገንዘብ ውሳኔ ትክክል መስሎ ካልተሰማዎት፤ ማስታወሻው ወይም ደብዳቤው በደረስዎ በ15 ቀናት ውስጥ፤ ጉዳዮ እንደገና እንዲታይሎት የስራ አገልግሎት ሚኒስቴርን (DOES ) መጠየቅ ይችላሉ። በሚቀጥለው ጽሁፍ እንደተገለጸውም፤ ወደ አስተዳደር ችሎት ጽህፈት ቤትም (Office of Administrative Hearings) ጉዳዮ እንዲሰማሎት አቤቱታ ማቅረብ ይችላሉ።

ጥያቄዎ ተቀባይነት አላገኘም የሚል ደብዳቤ **ከማመልከቻ መርማሪውና ውሳኔ ሰጪ** (Determination by Claims Examiner) ከደረስዎ ደግሞ ወደ የአስተዳደር ችሎት ጽህፈት ቤት (Office of Administrative Hearings) በኦንላይን online ወይም በስልክ ቁጥር (202) 442-9094 በመደወል አቤቱታዎን ማቅረብ ይችላሉ። አቤቱታዎን ለማቅረብ የሚሰጦት ቀናት 15 ቀናት ብቻ ነው። ይሁንና ይሄው የአስተዳደር ችሎት ጽህፈት ቤት (Office of Administrative Hearings)፤ የስራ ማጣት ክፍያ አቤቱታ የሚቀርብበትን ቀን በተመለከተ፤ የወረርሽኝ በሽታው ካለቀ በኋላ እስከ 30 ቀናት ድረስ አራዝሞታል።

በገንዘባዊ ውሳኔ ( Monetary Determination) የስራ ማጣት ክፍያ ለማግኘት ብቁ አይደሉም ከተባሉ በኋላ፤ አቤቱታ ማቅረብ እንደሚሻሎት ወይም በወረርሽኝ በሽታ ምክንያት ስራቸውን ላጡ የሚደረግ ክፍያ ለማግኘት ማመልከት ይሻሎታል ወይስ አይሻሎትም ለመወሰን በስልክ ቁጥር (202) 628-1161 ወይም በኦንላይን online በመግባት ሊጋል ኤድ( Legal Aid) ነጻ ምክር እንዲሰጦት አመልክቱ።

## <u>የሚሰጥ የክፍያ ልክ</u>

### በዚህ ከስራ ለውጡ የሚሰጠው ክፍያ (unemployment benefits) እኔ ስንት ነው ማግኘት የምችለው?

ያገኙት የነበረውን ገቢ ቢያንስ ከፊሉን ለመሸፈን፡ ከስራ ለወጡ የሚሰጠው መደበኛ ክፍያ በአጠቃላይ (unemployment benefits) **በሳምንት እስከ $444** ይደርሳል። በሳምንት ውስጥ የሚሰጠው አነስተኛው ገንዘብ $50 ነው። ከ ሚያዝያ እስከ ሓምሌ 31ቀን 2020 ደግሞ ክፍያ ለመቀበል ብቁ የሆኑ ሰራተኞች በየሳምንቱ ሌላ ተጨማሪ $600 ያገኛሉ። (ይህም በወረርሽኝ አደጋው ምክንያት መንግስት ከሚያደርገው የስራ መውጣት ክፍያ (unemployment Federal Pandemic Unemployment

Compensation or FPUC) ውስጥ ቢያንስ $1 እንኳን ለማግኘት ብቁ ሆነው ለተገኙ ሰራተኞች የሚሰጥ እርዳታ ነው።

ለመደበኛው የስራ ማጣት ክፍያ ሳይሆን ለዚህ **በወረርሽኝ አደጋ ምክንያት ስራቸውን ላጡ ሰራተኞች የሚሰጥ ክፍያ** (Pandemic Unemployment Assistance, or PUA) ብቁ የሆኑ ቢያንስ በሳምንት **$180** ያገኛሉ። ስለዚህ በየሳምንቱ የሚከፈሉት ገንዘብ ወደ ከፍተኛው $444 ከፍ እንዲል፤ ሰራተኞች በ2019 ያስገቡትን ገቢ የሚያሳይ የማረጋገጫ ዶኩመንቶችን ( ለምሳሌ ግብር የከፈሉበት ዶኩመንት ወይም ሌሎች ዶኩመንቶችን) ማቅረብ አለባቸው።

**ይሄ ከስራ የመውጣት ክፍያ እስከ ስንት ግዜ ይቆያል?**

እነኚህ መደበኛ የስራ መውጣት ክፍያ(Standard unemployment) ና በወረርሽኝ በሽታ ምክንያት ከስራ ሲወጡ የሚከፈል ክፍያ ( Pandemic Unemployment Assistance benefits)፤ ሰራተኛው ብቁ እስከሆነ ድረስና የሚስጠውን ካርድ በየሳምንቱ እስካስመዘገበ ድረስ ለ**39 ሳምንታት** ይዘልቃሉ። ይሁንና ይሄ በወረርሽኝ በሽታ ምክንያት ከስራ ሲወጡ የሚከፈል ክፍያ ( Pandemic Unemployment Assistance benefits) ምንም እንኳን ሰራተኛው የሚከፈልባቸውን 39 ሳምንታቱን ባይጨርስም፤ በ 2020 በታህሳስ ወር መጨረሻ ላይ ያከትማል።

በወረርሽኝ በሽታ ምክንያት ከስራ ሲወጡ ከሚከፈለው ክፍያ ( Pandemic Unemployment Assistance benefits) በተጨማሪ በየሳምንቱ የሚሰጠው $600 ከሚያዝያ ወር እስከ ሓምሌ 31ቀን 2020 ብቻ የሚዘልቅ ነው።

**የስራ ቦታዬ እንደገና ተከፍቷል። እኔ ግን አሁን ፓርት ታይም (part-time) ወይም በግማሽ ግዜ ነው በመስራት ላይ ያለሁት። ይህንን ከስራ ለወጡ የሚሰጠውን ክፍያ( unemployment benefits) አሁንም ማግኘት እችላለሁን ?**

ምናልባት። አጠቃላይ ገቢዎ (ማለትም ግብር ሳይቆረጥበት የሚያገኙት ደሞዝ) ምን ያህል እንደሆነና በየሳምንቱም ምን ያህል ገንዘብ እንደሚያገኙ ለስራ አገልግሎት ሚኒስቴር (Department of Employment Services) በሳምንታዊ ካርዶ ያስታውቁ። ይህንንም በሚከፈሉበት ሳምንት ሳይሆን፤ በዛ በሰሩበት ሳምንት ማስታወቅ አለቦት።

ስለዚህ የስራ አገልግሎት ሚኒስቴር (Department of Employment Services) ፤ ስራ በሚሰሩባቸው በከፊል ግዝያቶች ምን ያህል ክፍያ ማግኘት እንዳለቦት ለመገምገም የሚያስችለውን አገባብ ተጠቅሞ፤ የሚገባዎትን ይከፍሎታል። የሚጠቀምበት አገባብም፣

**አንድ፤** በየሳምንቱ በሚያገኙት ክፍያ ላይ $50 ይጨምርበታል
**ሁለት፤** (ግብር ከመቆረጡ በፊት) የሚያገኙትን አጠቃላይ ሳምንታዊ ገቢ በ0.66 ያባዛል
**ሶስት፤** ከአጠቃላይ ገቢዎ 66%ውን ወስደው (በቁጥር ሁለት ላይ ያለው) በየሳምንቱ በሚያገኙት ክፍያ ላይ $50 (በቁጥር አንድ ላይ ያለው) ጨምረው ቢያወዳድሩ የትኛው እንደሚተልቅ ይመልከቱ።

የቁጥር አንድ ስሌት በቁጥር ሁለት ላይ ከተደረሰው ቁጥር ከበለጠ፤ በቁጥር አንድና በቁጥር ሁለት መካከል ያለውን የገንዘብ ልዩነት ለማግኘት ብቁ ኖት ማለት ነው።

በቁጥር ሁለት ላይ ያለው ቁጥር፤ በቁጥር አንድ ላይ ካለው ቁጥር ከበለጠ፡ የስራ መውጣት ክፍያ (unemployment benefits) ለማግኘት ብቁ አይደሉም ማለት ነው።

## ከስራ የመውጣት ክፍያ ( unemployment benefits) ማግኘቴ ለምሳሌ እንደ ስናፕ የምግብ እርዳታ ( SNAP) ከመሳሰሉት ድርጅቶች የማገኘውን ጠቀሜታ ሊጎዳ ይችላልን ወይም ሜዲኬድ (Medicaid )ማግኘቴን መቀጠል እችላለሁን ?

መደበኛው ከስራ የመውጣት ክፍያ (Standard unemployment benefits) ና ከወረርሽኝ በሽታው ጋር የተያየዙ ግዜያዊ ክፍያዎች፤ በአብዛኛዎቹ በዲሲ ሰራተኞች ህዝባዊ የጠቀሜታ ፕሮግራሞች በኩል እንደ ገቢ ነው የሚቆጠሩት።

አብዛኛውን ግዜ ፉድ ስታምፕ( food stamps) በመባል የሚታወቀው የምግብ ኩፖን ወይም **ስናፕ** (SNAP) እና ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ቤተሰቦች የሚደረግ የገንዘብ እርዳታ **የቲ-ኤ-ኤን-ኤፍ** (TANF)፤ ወይም በ ፒ-ዩ-ኤ( PUA) ክፍያዎች ና በኤፍ-ፒ-ዩ-ሲ (FPUC) አማካኝነት በየሳምንቱ የሚሰጠው ተጨማሪ የ$600 ክፍያ ሁሉ እንደገቢ ይቆጠራሉ። ይህም ማለት ከስራ የመውጣት ክፍያ ሲያገኙ፡ ከ**ስናፕ** (SNAP ) የሚያገኙትን ክፍያ በጣም ዝቅ ሊያደረገው ይችላል ማለት ነው። ምናልባትም እስከ ዜሮ ሊያደርሰው ይችላል። ይህም ከ**ቲ-ኤ-ኤን-ኤፍ** (TANF) ክፍያ ለማግኘት ብቁነትዎን ይሰርዛል ማለት ነው።

**ሜዲኬድ**ን( Medicaid) በተመለከተ ደግሞ ከስራ ለወጡ ሰራተኞች የሚከፈለው መደበኛ ክፍያ (unemployment benefits) እና በወረርሽኝ በሽታ ምክንያት የሚከፈለው የስራ መውጣት ክፍያ እንደ ገቢ ይቆጠራሉ። ይህ በተጨማሪ በየሳምንቱ የሚሰጠው የ $600 ክፍያ ግን እንደ ገቢ አይቆጠርም። ይሁንና ዲሲ፤ ከሜዲኬድ ተቀባዮች ይጠይቀው የነበረ በቤት ውስጥ አንዳች ለውጥ ቢደረግ ሪፖርት ማድረግ አለባችሁ የሚለውን ሰርዞታል። ይሄው ህዝባዊ የወረርሽኝ አደጋ ካበቃም በኋላ ብቁነት እስከ 60 ቀናት ድረስ እንዲራዘም አድርጓል። ስለዚህ አሁን **ሜዲኬድ** (Medicaid) በማግኘት ላይ ከሆኑ፤ በቤትዎ ውስጥ ምንም ዓይነት ለውጥ ቢመጣ ሪፖርት ማድረግ የለቦትም። ብቁነትዎም እንዳለ ይቀጥላል።

ከስራ ስለወጡ የሚከፈሎት መደበኛ ክፍያም ሆነ ይሄ በተጨማሪ ከ FPUC በየሳምንቱ የሚሰጦት የ$600 ክፍያ **የሶሽያል ሴኩሪቲ የጡረታ ክፍያዎን** (Social Security benefits)ም ሆነ በስንክልናዎ ምክንያት የሚያገኙትን የስንክልና ክፍያ (SSDI) አይነካውም፣ አይቀንሰውምም።

ከስራ ስለወጡ የሚያገኙት ክፍያና በየሳምንቱ በተጨማሪ የሚሰጦት የ$600 ክፍያ በ **ተጨማሪ የደህንነት ገቢ** (Supplemental Security Income (SSI) ውስጥ ያልሰሩበት ገቢ ተብሎ ይታሰባል። በመሆኑም የእነዚህ ክፍያዎችን ዝርዝር ሪፖርት በየግዜው ለሶሽያል ሴኩሪቲ ጽህፈት ቤት መስጠት ይኖርቦታል።

ህዝባዊ ጠቀሜታዎችን በሚመለከት ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ የህዝብ ጠቀሜታ የጥያቄና መልስ [Public Benefits FAQs] ይጎብኙ።

**በዲሲ የቤቶች ባለስልጣን በሚተዳደሩ የህዝብ ቤቶች ፕሮግራሞች** ደግሞ መደበኛው የስራ ማጣት ክፍያ እንደ ገቢ ስለሚቆጠር፡ ለቤት ኪራይ በሚከፍሉት ገንዘብ ላይ ለውጥ ሊያደርግ ይችላል። ይሁንና በየሳምንቱ በተጨማሪ የሚከፈልዎ $600 እንደ ገቢ ስለማይቆጠር ለቤት ኪራይ በሚከፍሉት ላይ ለውጥ አያመጣም።

**ክልክ በላይ የተከፈለ**

**ከአሁን ቀደም ከሚገባኝ በላይ ስለተከፈልኩ፤ ይህንን አሮጌውን ክፍያ መልሶ ለመክፈል፤ በአሁኑ ወቅት የማገኘው ከስራ የመውጣት ክፍያዬ ተይዞብኛል። ምን ማድረግ እችላለሁ ?**

ማግኘት የነበረቦት ከስራ መውጣት ክፍያ፤ ከልክ በላይ የተከፈለ ያለፈ ክፍያን ለማጣጣት ከተያዘቦት፤ በመጀመርያ፤ የስራ መቀጠርያ አገልግሎት ክፍል( Department of Employment Services )በጽሁፍ ሊያሳውቆት ይገባል።ይህ ማሳወቅያ **የገንዘብ ማጣጣት ማስታወቅያ** (Notice of Recoupment) በመባል ይታወቃል። ይህንን በተመለከተ፡ በተለይም (1) ከልክ በላይ የተከፈሉት በእርስዎ ጥፋት ካልሆነ ና (2) ገንዘቡ ሊቆረጥቦት እንደማይገባ ማረጋገጥ ከቻሉ በሚቀጥሉት አስራ አምስት ቀናት ውስጥ ለአስተዳደር ፍርድ ጽህፈት ቤት (Office of Administrative Hearings ) አቤቱታዎን ማቅረብ መብትዎ ነው።

በእንደዚህ ባለ ሁኔታ ዲስትሪክቱ የሚፈቅደው፤ ከስራ ስለወጡ ከሚያገኙት ክፍያ ከ50% የማይበልጥ ተቆራጭ ብቻ ነው ማድረግ የሚቻለው፤ በአንዳንድ ሌሎች ቦታዎች ደግሞ ከዛ በታች ነው።

**ጉዳዮን የሚቀይር ማስታወሻ** (Offset Notice) ወይም **ከልክ በላይ ተከፍሎታል የሚል የውሳኔ ወረቀት** (Notice of Determination of Overpayment) ከደረሶት፤ በስልክ ቁጥር (202) 628-1161 ወደ ሊጋል ኤድ (Legal Aid) በመደወል ወይም ኦንላይን online በመግባት ነጻ የእርዳታ አገልግሎት እንዲያገኙ ማመልከት ይችላሉ

**የህዝብ ዕዳ ክፍያ**

**ከስራ የመውጣት ክፍያ** (unemployment benefits ) **ለማግኘት ሳመለከት፤ በህዝብ ዕዳ ክፍያ ህግ (public charge) መሰረት ነገሩ ከጥቅሜ ውጭ ሊሆን ይችላልን?**

አይችልም። ከስራ የወጡ ስደተኞች፤ ከስራ የወጡበትን ክፍያ ለማግኘት ማመልከቻ ሲይቀርቡ፤ በአገር ውስጥ የሚኖሩበት ሁኔታ እንዲስተካከለላቸው በሚጠይቁበት ወቅት የህዝብ ዕዳ ክፍያ ውሳኔ ግምት ውስጥ አይገባም።

***

ጉዳዮን በሚመለከት አንዳች ምክር ቢያስፈልጎት፤ ከሊጋል ኤድ (Legal Aid) ጋር ተገናኙ። በሰሜናዊ ምዕራብ( Northwest ) ና በደቡባዊ ምስራቅ(Southeast) ያሉት ጽህፈት ቤቶቻችን ለህዝብ ዝግ ናቸው። ይሁንና በስልክና በኦንላይን ከእኛ ጋር መገናኘት ይችላሉ። የኛን አገልግሎት ለማግኘት በስልክ ቁጥር (202) 628-1161 በመደወል ወይም online በመግባት ያመልክቱ።